# የሕግ ቅድስና ሆይ ወዴት ነሽ

www.ethiopiansemay.blogspot.com

**ከወሰን ሰገድ ገ/ኪዳን (ጋዜጠኛ )**

የምፅአቷ ቀን ግም ያለች እንደሆን፣

የነፍስ ዛንዚራን፣ የህይወት ብረት መዝጊያ…

አድኖም-አያድን፤

ሱባዔም አያግዝ፣ ሥጋ-ወደሙ አይሆን፣

አሁን ነው ንስሐ፣ አሁን ነው መፀለይ፣

ዛሬ ነው መመነን፤

አሉ- አሉ መምህሩ

የነፍስ ልጃቸውን ሲመከሩ-ሲዘከሩ፡፡

- ታምራት ላይኔ

የቀድሞው ም/ጠ/ሚ/ር ታምራት ላይኔ "ስኳር በመላስ" ተከስሰው እስር ቤት ከገቡ ከአምስት ዓመት በኋላ ማለትም በ1994 ዓ.ም የሕግንና የፍትህ ሥርአትን ምንነት በጥልቀት የሚፈትሽ

የመከራከሪያ ፅሁፍ ለጠቅላይ ፍርድ ቤት አቅርበው ነበር፡፡ ይህንን መከራከሪያቸውን“ዜጋ” መፅሔት በታህሳስ/ጥር 1994 ዓም ዕትሙ “ሲቀብሩ ብትደርስ አፈር ለግስ” የሚል ርዕስ ሰጥቶ ለንባብ አበቃው፡፡ ያንን የአቶ ታምራት የመሟገቻ ፅሁፍ በርካታ የሕግ ባለሙያዎች ለሰነድነት ይፈልጉት እንደነበርም አስታውሳለሁ፡፡ ከላይ ለመንደርደሪያነት የተጠቀምኩበት ግጥም፣ የመከራከሪያ ፅሁፋቸው ማሳረጊያ እንዳደረጉት ነው “ዜጋ” መፅሔት የሚያመላክተው፡፡

አቶ ታምራት እስር ቤት ሆነው ለጠ/ፍ/ቤት ያቀረቡት የመሟገቻ ፅሁፍ “ፍትህ አገኛለሁ ብዬ አላምንም” የሚል አንደምታ ያለው ነበር፡፡ በዚያ መረር እና ከረር ባለ መሟገቻ ፅሁፋቸው ውስጥ በጥብቅ የማምንበት አቋሜ ነው ሲሉ በማጣቀሻነትና በአስረጅነት ያጣቀሱት፣ ዕውቅ የሕግና የፍልስፍና ምሁር የሆኑት (Joan Rawels) ጆን ራወልስ Theory of Justice በሚል ርዕስ ካሳተሙት መፅሐፍ(የ1971 ዕትም ገፅ 3) በመዋስ ነው፡፡ እኔም እሳቸው ለመሟገቻቸው ማዳበሪነት የተዋሱትን ሃሳብ ትርጉም እንዳለ ለመዋስ ነው ከ10 ዓመት በላይ የኋሊት በትውስታ የተመለስኩት፡፡ እነሆ፡-

“…የማሕበራዊ ተቋማት ቀዳሚው ቅድስና ፍትህ ሲሆን፣ የአስተሳሰብ ሥርዓት ቅድስና ደግሞ እውነት ነው፡፡ አንድ ንድፈሃሳብ የቱንም ያህል ውበትና ጠቀሜታ ቢኖረው፣ እውነት እስካልሆነ ድረስ እንዲወድቅ ወይም እንዲሻሻል መደረግ ይኖርበታል፡፡ እንደዚያውም ሁሉ ሕጎችና ተቋሞች ምንም እንኳ በውል የተደራጁና ቀልጣፋ ቢሆኑም፣ ኢ-ፍትሃዊ እስከሆኑ ድረስ ሊስተካከሉ ወይም ሊሻሩ ይገባል፡፡ እያንዳንዱ ሰው የሕብረተሰቡ ብልፅግና (ወይም ደህንነት) በአጠቃላይ እንኳ ሊከላው የማይችል የማይገሰስ መብት አለው፡፡ በዚህም የተነሳ ጥቂቶች ነፃነታቸውን ቢያጡም ሌሎች በሚቀዳጁት የላቀ ጠቀሜታ ሊስተካከል ይችላል የሚለውን አስተሳሰብ የፍትሕ መርሆ አይቀበለውም፡፡ ጥቂቶች እንዲከፍሉ የሚጫንባቸውን መስዋዕትነት አይፈቅድም፡፡ በመሆኑም ፍትሃዊ ሕብረተሰብ ውስጥ የእኩሎች ነፃነት እንደቅቡል የሚወሰድ ነው፡፡…በፍትህ የተረጋገጡ መብቶች ለፖለቲካ እሰጥ አገባ የሚቀርቡ ወይም በማሕበራዊ ፍላጎቶች ሥር የሚወድቁ

አይደሉም፡፡… የሰው ልጆች እንቅስቃሴ ቀደምት ቅድስናዎች የመሆናቸውን ያህል እውነትና ፍትሕ ለድርድር የማይቀርቡ ናቸው፡ ፡…”

እንደ እውነቱ ከሆነ ስለሕግ ጥልቅና የመጠቀ ዕውቀት የለኝም፡፡ የሕግ ባለሙያዎች “ህግን አለማወቅ ከተጠያቂነት አያድንም” የሚሉ መሰረታዊ መርህ እንዳላቸው ግን እውቃለሁ፡፡ ሕግን አለማወቅ ከተያቂነት አያድንም የሚባለው በምን የተነሳ ነው? አባባላቸው ታሪካዊ ዳራ አለው፡፡ ከ4ሺ ዓመታት በላይ ወደኋላ የሚሻገር፡፡ ከባቢሎኑ ገዢ ከንጉሥ ሐሙራቢ (ከክርስቶስ ልደት 1800 ዓመት በፊት) ጀምሮ የነበሩ ጥንታዊ ሐጋጊያን (ሕግ አውጪዎች) ማንኛውም ተራ ሰው ሕግን እያነበበ እንዲረዳና እንዲከተል ለማድረግ በትልልቅ ድንጋያማ ሰሌዳ ላይ እየቀረፁ ያስቀምጡ እንደነበር ነው ታሪክ የሚዘክረው፡፡ በዚህም የተነሳ ነው “ሕግ አላውቅም ማለት መከላከያ አይሆንም” የሚባለው፡፡ ይህ አባባል የሚመለከተው ግን ተራ-ተርታውን ሰው ብቻ አይመስለኝም፡- ሕግ አውጪዎችን፣ ሕግ ተርጓሚዎችን እና ሕግ አስፈፃሚዎችን ጭምር እንጂ፡፡

እንዲያ ከሆነ ዘንዳ የሕግ ገዢነት መሠረት መንትያ የ“ቅድስና” ምሶሶዎች ላይ የቆመ ነው ማለት እንችላለን፡፡ እነሱም፣ “የአስተሳሰብ ስርዓት ቅድስና” እና “የማህበራዊ ተቋማት ቅድስና” ናቸው ብዬ አምናለሁ፡፡

## ***<u>ቅድስና ሆይ ወዴት ነሽ!?</u>***

ቅድስና የሚለው ቃል ሲነሳ ቀድሞ ወደህሊናችን የሚመጣው መንፈሳዊ እሳቤ ነው፡፡ በእርግጥም ቃሉ ከመንፈሳዊው አስተሳሰብ ጋር ተዛማጅነት አለው፡፡ ከክፋት የተለየ፣ ንፅሕና፣ ግብረገብነት፣ ብሩክነት …የሚል ፍቺ እንዳለው ነው ቀደምት የአማርኛ መዝገበ ቃላት የሚያመለክቱት፡፡

ልክ እንደዚያው ሁሉ፣ ማንኛውም ሕግ ቅድስና ሊኖረው ይገባል፡፡ ከክፋት የተለየ፣ ግብረገብነት የተላበሰ፣ ብሩክነት ወይም ሠናይ

ውጤት ሊያመጣ የሚችል መሆን እንዳለበት መናገር ለቀባሪው እንደማርዳት ያለ ፌዝ ነው፡፡ በሌላ አገላለፅ ሕግ አንድን ሕብረተሰብ ማለትም ከሊቅ እስከደቂቅ፣ ከሹም እስከሹምባሽ፣ ከቁንጮ ባለሥልጣን እስከተራተርታ ዜጋ ወዘተ በርቱዓዊነት የሚያገለግል (ሠላማዊ) መሳሪያ ሊሆን ይገባል፡፡

ይህ ማለት ማንኛውም ሕግ አይሻሻልም ወይም አዲስ ሕግ መውጣት የለበትም ማለት አይደለም፡፡ ነገር ግን ነባሩ ሕግ በሚሻሻልበት ወይም አዲስ ሕግ በሚወጣበት ጊዜ ማህበራዊ ቅቡልነትና ርትአዊ ውጤት ይኖረው ዘንድ ግድ ይላል፡፡ ሕግ አንዱን ወገን አክብሮ ሌላውን ወገን ካከሰረ ሚዛናዊነቱ ጥያቄ ምልክት ውስጥ ይወድቃል፡፡ ቅድስናውን ያጣል፡፡ ቅድስና የሌለው ሕግ እንደአጭበርባሪ ነጋዴዎች ሚዛን ልኩን ይስታል፤ ያሳስታል፡፡ ቅድስና የሌለው ሕግ ሰብዓዊነቱንም ይስታል፡፡ ሰብዓዊ ያልሆነ ሕግ ደግሞ ከጠቀሜታው ይልቅ ጉዳቱ ያመዝናል፡፡ ክፋቱ ይበረታል፡፡ ቅድስና ሆይ ወዴት ነሽ? ያሰኛል፡፡ ከቅርብ ዓመታት ወዲህ በሃገራችን እየታየ ያለው የሕግ ጉዳይም የሕግን ቅድስና ጥያቄ ምልክት ውስጥ እየከተተ ያለ ይመስለኛል፡፡ ለዚህም ባለፉት አራት አመታት ውስጥ የፀደቁትንና በተግባር ላይ እየዋሉ ያሉትን ጥቂት የሕግ ድንጋጌዎችና አተገባበራቸው (የፕሬስ ሕግ እና የፀረ ሽብር ሕግ ..ወዘተ) የሕግን ንፅህና ጥያቄ ምልክት ውስጥ የከተቱ መሆናቸው በአስረጅ ማመላከት የሚቻል ይመስለኛል፡፡

አዲሱ የፕሬስ ሕግ በሥራ ላይ ከዋለ በኋላ የፕሬሱ ዓለም ህይወት ከድጡ ወደማጡ መፍገምገምገሙ የአደባባይ ምስጢር ነው፡፡ ነፃው ፕሬስ መቃብሩ ተምሶለት ቀብሩን ለመፈፀም አፈር ማልበስ ብቻ ነው የቀረው ብንል ማጋነን አይሆንም፡፡ መንግስታዊው የሕትመት ተቋም የግል ፕሬስን ላለማተም የቆረጠበት ዘመን ላይ ነው፡፡ ይህ ሁኔታ በራሱ የማሕበራዊ ተቋማትን ቅድስናን ጥያቄ ምልክት ውስጥ የሚከት ነው፡፡ ይህ ብቻ አይደለም፤ የፕሬስ ሕጉን የቅድስና ተልዕኮ ያረከሰም ይመስለኛል፡፡

የፀረ-ሽብር ሕጉም ቢሆን እንዲሁ ቅድስናዊ ውጤቱ ወይም ተልዕኮ አነጋጋሪ እየሆነ ነው፡፡ ሕጉ ሥራ ላይ መዋል ከጀመረ ወዲህ ለፍ/ቤት የሚቀርቡ ክሶች ሁሉ ሽብርና አሸባሪነት ይሁኑ የተባለ ይመስላል፡፡ ጋዜጠኞች፣ በሃገር ውስጥ በሠላማዊ መንገድ እየታገሉ

ያሉ የፖለቲካ ድርጅቶች አመራሮችና አባላቶቻቸው፣ የሕዝበ ሙስሊሙ የመብት ጥያቄ አቀንቃኞች…ወዘተ ወዘተርፈ በዚሁ ሕግ ተከሰዋል፡፡ ገሚሶቹ በክርክር ላይ ሲሆኑ፣ ገሚሶቹ ደግሞ የበርካታ አመታት፣ ዕድሜ ልክ እስራት እና የሞት ፍርድ ጭምር ተፈርዶባቸዋል፡፡

የዚህ ፅሁፍ ዓላማ ክሱም ሆነ ፍርዱ ትክክል ነው ወይም አይደለም ለማለት የሚዳዳ አይደለም፡፡ የክሱን ሂደትና ፍርድ ሳይሆን፣ የሕጉን አሉታዊ እና አዎንታዊ ውጤት በደምሳሳው ለመቃኘት ነው የሚሞከረው፡፡ በአጭሩ የሕግን አዎንታዊ ውጤት ማጠየቅ ነው፡፡ ለዚህም ይረዳን ዘንድ አብነት የምናደርገው በእነ አቶ አንዱዓለም አራጌ እና ጋዜጠኛ እስክንድር ነጋ ላይ የተሰጠውን የፍርድ ውሳኔ ተከትሎ መንግስት(ዓቃቤ ሕግ) ያቀረበውን የውርስ ክስ ነው፡፡

እንደሚታወቀው እነ አቶ አንዱዓለም አራጌ እና ጋዜጠኛ እስክንድር ነጋ በቀረበባቸው ክስ (በፀረ-ሽብር ሕጉ) ፍ/ቤት ጥፋተኛ ናችሁ ብሏቸዋል፡፡ አንዱዓለም አራጌ በዕድሜ ልክ ጋዜጠኛ እስክንድር ነጋ ደግሞ በ18 ዓመት እስራት እንዲቀጡ ወስኗል፡፡ ከሳሽ ወገን ይህ ፍርድ አልበቃ ብሎት ሃብት ንብረታቸው ጭምር ሊወረስ ይገባል ሲል ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት 4ኛ ወንጀል ችሎት አቤቱታ! አቅርቧል፡፡

ዓቃቤ ሕግ በ1ኛ ተከሳሽ አንዱዓለም አራጌ ባለቤት ስም የተመዘገበ የቤት መኪና፣ በ7ኛ ተከሳሽ ጋዜጠኛ እስክንድር ነጋ ስም የተመዘገበ ቤት እና ከእናቱ በውርስ ያገኘውን ሌላ ቤት እንዲሁም በባለቤቱ ጋዜጠኛ ሰርካለም ፋሲል ስም የተመዘገበ የቤት መኪና እና በ16 ተከሳሽ አበበ በለው ስም የተመዘገበ ቤት ሊወረስ ይገባል ሲል ነው አቤቱታ ያቀረበው፡፡ ክሱ ከቀረበባቸው ሰዎች መሃል ጋዜጠኛ እስክንድር ነጋ እና ባለቤቱ ሰርካለም ሊወረሱብን አይገባም ብለው እንደማይሟገቱ ጉዳዩን ለያዘው ፍ/ቤት ማሳወቃቸው ተነግሯል፡፡ የአንዱዓለም አራጌ ባለቤት ግን ይወረስ የተባለው መኪና ለእስረኛው የትዳር ጓደኛቸው ስንቅና ልጆቻቸውን ት/ቤት ማመላለሻ እንደሚገለገሉበት ገልፀው እየተከራከሩ መሆኑን መገናኛ ብዙሃን ዘግበዋል፡፡

የሆነ ሆኖ ይህ ፅሁፍ ይህ የውርስ አቤቱታ መጨረሻው ምን ሊሆን ይችላል? በሚለው ጉዳይ ላይ የሚያተኩር አይደለም፡፡ ቀድሞ ነገር ክሱ መመስረት ነበረበት ወይ? የሚል መጠይቅ ላይ ነው የሚያጠነጥነው፡፡ ከሳሽ ወገን ከዚህ የውርስ አቤቱታ የሚያተርፈው ወይም ሊያተርፍ የሚፈልገው ውጤት ምንድነው? ክሱ ሲመሰርት ለአጠቃላይ ማሕበረሰቡ ሊያስተላልፍ የሚችለው ሰናይ መልዕክት ምንድነው? ወይም ምን ሊሆን ይችላል? ነው ጥያቄው፡፡....ብላ! ብላ! ብላ!

እኔ እስከሚገባኝ የማንኛውም ሕግ ውጤታማነት የሚለካው ወይም መላካት ያለበት ጥፋተኛ የተባለውን ወገን በመቅጣት ብቻ አለመሆኑ ነው፡፡ ለማሕበረሰቡ መልካምና ቅቡል መልዕክት ማስተላለፍም ጭምር እንጂ፡፡ ሕግ ጥፋተኛ የተባለውን ወይም ሆኖ የተገኘውን ሰው ከመቅጣት ባሻገር፣ የተቀጪውን ሰው ቤተሰብና ልጆች ሁሉ አብሮ የሚቀጣ መሆን የለበትም፡፡ አንድን ሰው በ18 እና በዕድሜ ልክ እስራት ከመቅጣት የበለጠ ቅጣት ምን አለ? በአንድ ግለሰብ ጥፋት የተነሳ (ጥፋት ከተባለ) በጉዳዩ ውስጥ የሌሉበት የትዳር ተጓዳኞችና ልጆች የእኔ የሚሉት ሃብትና ንብረት እንዲያጡ መደረግ አለበት ወይ? በግለሰቡ የተነሳ ሌሎች ሠዎች በተፈጥሮ ያገኟቸውን የመኖር መብታቸውን እንዳይጠቀሙበት ለማድረግ መጣር ተገቢ ነው ወይ? ወዘተ ብለን ብንጠይቅ መልሱ አንድና አንድ ነው የሚሆነው፡- ማጣት የለባቸውም የሚል፡፡

"...እያንዳንዱ ሰው የሕብረተሰቡ ብልፅግና (ወይም ደህንነት) በአጠቃላይ እንኳ ሊከላው የማይችል የማይገሰስ መብት አለው፡፡ በዚህም የተነሳ ጥቂቶች ነፃነታቸውን ቢያጡም ሌሎች በሚቀዳጁት የላቀ ጠቀሜታ ሊስተካከል ይችላል የሚለውን አስተሳሰብ የፍትሕ መርሆ አይቀበለውም፡፡ ጥቂቶች እንዲከፍሉ የሚጫንባቸውን መስዋዕትነት አይፈቅድም...." የሚለው የሕግና የፍልስፍና ምሁሩ ፕሮፌሰር ጆን ራወልስ ትንታኔ የሚያመለክተው፣ ሕግ የሰው ልጆችን መሰረታዊ መብት በምንም ዓይነት ሁኔታ የሚሸረሽር ወይም የሚነካ መሆን እንደሌለበት ነው፡፡

ለምሳሌ ያህል የአንዱዓለም አራጌ እና የጋዜጠኛ እስክንድር ነጋ ሐብት እና ንብረት ቢወረስ በልጆቻቸው ህሊና ውስጥ የሚቀረው

ወይም የሚቀረፀው ነገር ምንድነው? እነዚህ ህፃናት ልጆች የነገው ትውልድ አስባለሁ፤ ናቸውም፡፡ ሕግ ደግሞ የነገውን ሃገር ተረካቢ ትውልድ የመንከባከብ የውዴታ ግዴታ አለበት፡፡ እናም ውርሱ (የውርስ አቤቱታው) ለቀጣዩ ትውልድ የሚያስተላልፈው መልካም መልዕክት ምንድነው?

እንደኔ እምነት የውርስ አቤታቱው በራሱ የሕግን ቅድስና ለቀጣዩ ትውልድ የሚያስተላልፍ አይመስለኝም፡፡ ሕግ “ለፖለቲካ እሰጥ አገባ የሚቀርብ ወይም በማሕበራዊ ፍላጎቶች ሥር የሚወድቅ አይደለም፡፡…” የሚባለው ለዚህ ይመስለኛል፡፡ ሕግ - ለቀጣዩ ትውልድ ማንነትና ህልውና አብዝቶ መጨነቅ አለበት፡፡ ሕግ - በቀጣዩ ትውልድ ህሊና ውስጥ ጥላሸት የሚቀባ መሆን የለበትም፡፡ ስለዚህም ነው ቅድስና ሆይ ወዴት ነሽ? ለማለት የተገደድኩት፡፡

ከመክሰስና ከመካሰስ፣ ከመፍረድና ከመፋረድ ባሻገር ለትውልድና ለሀገር የሚበጀው የሕግን ቅድስና በዘላቂነት መጠበቅ እና ማስጠበቅ ነው፡፡

“አሁን ነው ንስሐ፣ አሁን ነው መፀለይ፣

ዛሬ ነው መመነን፤

አሉ- አሉ መምህሩ

የነፍስ ልጃቸውን ሲመከሩ-ሲዘከሩ…” እንዲሉ አቶ ታምራት ላይኔ፡፡